

AMHARIC

# የኪቪድ-19 ክትባቶች፡ በብዛት የሚጠየቁ ጥያቄዎች

ይህ ጽሑፍ፡ **ትክክለኛ የሕክምና መረጃ** በመስጠት፡ **በእውቀት ላይ የተመሠረተ ውሳኔ** እንዲወስኑ የሚያግዝ ነው። በሐኪሞች ተገምግሟል። ይህ እስከ መጋቢት 2021 ድረስ ያለ በጣም ወቅታዊ መረጃ ነው እንደ አስፈላጊነቱም ይዘመናል።

---

## ክትባቶቹ በጥቁሮች ወይም በሌሎች አናሳ ማህበረሰቦች ላይ ተሞክሯል?

የክትባት ጥናቶች ላይ **20%-38% ጥቁሮች እና ሌሎች አናሳ ማህበረሰቦች ተካተው ነበር።**

## መጠነኛ ተጓዳኝ ጉዳቶች ኣጋጥመውኝ ከነበረ ለሁለተኛ ጊዜ ክትባቱን መውሰድ አለብኝን?

አዎ! መለስተኛ ተጓዳኝ ጉዳቶች በብዙ ሰዎች ላይ ይታያል። ሙሉ በሙሉ ሰውነትዎ በሽታውን እንዲከላከል ሁለት ጊዜ መከተብ ያስፈልግዎታል - **አንድ ዶዝ በቂ የመከላከያ አቅም አይሰጥዎትም።** ሰውነትዎ መጥፎ ምላሽ ከሰጠ፡ ስለዚህ ጉዳይ ከህክምና ባለሙያ ጋር መነጋገሩ የተሻለ ነው።

## መጥፎ አለርጂ አለብኝ፡ ክትባቱን ልውሰደው?

በክትባቱ ውስጥ ያሉ ንጥረ ነገሮች አለርጂ ካለብዎ ወይም ከዚህ በፊት ለሌላ ክትባት ሰውነትዎ መጥፎ ምላሽ ከሰጠ፡ ክትባቱን መውሰድ የለብዎትም። የሌሎች ነገሮች (ምግብ፣ መድኃኒቶች) አለርጂ ካለብዎ፡ **ከሕክምና ባለሙያ ጋር ይነጋገሩ።**

## የክትባቱ አሰጣጥ እንዴት ነው እንዲሁም በመጀመሪያ ክትባቱ የሚሰጠው ማን ነው?

የተለያዩ የክትባት አሰጣጥ ደረጃዎችን የሚያስተዳድር ቡድን (“የሰራተኛ-ኃይል”) አለን። ከኮቪድ-19 የተነሳ በጣም ሊታመሙ የሚችሉት በመጀመሪያ ክትባቱን ያገኛሉ፡ የጤና እንክብካቤ ሰራተኞች ፣ የረጅም ጊዜ እንክብካቤ ቤቶች ውስጥ የሚኖሩ ነዋሪዎች ፣ ወዘተ። የሚቀጥለው ደረጃ የጤና ችግር ያለባቸውን እና አዛውንቶችን ያጠቃልላል። **በ 3ኛ ደረጃ፡ መከተብ የሚፈልጉ ሰዎች ሁሉ ክትባቱን መውሰድ ይችላሉ።**

## እነዚህ ክትባቶች ከ 65 ዓመት በላይ ለሆኑ ሰዎች ይሠራሉ?

የ Pfizer-BioNTech እና የ Moderna ክትባቶች በወጣቶች ላይ ያሳዩትን የመከላከል አቅም፡ ዕድሚያቸው ከ 65 ዓመት በላይ በሆኑ ሰዎች ላይም ተመሳሳይ የመከላከል አቅም አሳይተዋል፡ ከ 65 ዓመት በላይ ለሆኑ ህመምተኞች **Pfizer-BioNTech 95% የመከላከል አቅምን የሰጠ ሲሆን Moderna ደግሞ የ 86%** የመከላከል አቅም ሰጥቷል።

## ክትባቱ፡ ኮቪድ-19 ሊያመጣብኝ ይችላል?

ክትባቶች ቫይረሱን እስከነህይወቱ የያዙ አይደሉም - ይህ ማለት በውስጣቸው ምንም ዓይነት ቫይረስ የላቸውም ፣ ስለሆነም በሰውነትዎ ው**ስጥ ኢንፌክሽን ሊያመጡ አይችሉም** ።

sherbourne HEALTH · REGENT PARK COMMUNITY HEALTH CENTRE · LOFT · CITY PARK CO-OPERATIVE APARTMENTS INC.



AMHARIC

# የኪቪድ-19 ክትባቶች፡ በብዛት የሚጠየቁ ጥያቄዎች

ይህ ጽሑፍ፡ **ትክክለኛ የሕክምና መረጃ** በመስጠት፡ **በእውቀት ላይ የተመሠረተ ውሳኔ** እንዲወስኑ የሚያግዝ ነው። በሐኪሞች ተገምግሟል። ይህ እስከ መጋቢት 2021 ድረስ ያለ በጣም ወቅታዊ መረጃ ነው እንደ አስፈላጊነቱም ይዘመናል።

---

## ክትባቴን ከወሰድኩ በኋላ አሁንም ማስክ መልበስ ያስፈልገኛልን? ለምን?

**አዎ።** አሁንም በኮቪድ-19 የመያዝ እና ለሌሎች የማስተላለፍ ዕድል በትንሹ አለ። **ክትባቱን ከወሰዱ በኋላ፡ አሁንም ማስክ ማድረግ እና ርቀትዎን መጠበቅ አለብዎት ።**

## ስለ ተጓዳኝ ጉዳቶች ብዙ መረጃ አለን?

የተከናወኑት ጥናቶች ጥሩ ውጤት ያሳያሉ፡ **ጥቂት ከባድ ተጓዳኝ ጉዳቶችም** ነበሩ። አብዛኛዎቹ ተጓዳኝ ጉዳቶች ክትባቱን ከወሰዱ ከ2-3 ቀናት ባለው ጊዜ ውስጥ እና 6 ሳምንታት እስከሚያልፍ ድረስ ይከሰታሉ። ጥናቶቹ ሲከናወኑ፡ **ሰዎች ክትባታቸውን ከወሰዱ በኋላ እስከ 2 ወር ድረስ ይከታተሏቸው ነበር ።**

## የረጅም ጊዜ ተጓዳኝ ጉዳቶችስ?

አሁንም ቢሆን Health Canada ገና የሚመጡ ሌሎች ተጓዳኝ ጉዳቶች አለመኖራቸውን ለማረጋገጥ፡ ክትባታቸውን የሚወስዱ ሰዎችን በመከታተል ላይ ነው። **አዲስ ተጓዳኝ ጉዳት ቢመጣ፡ በጣም አልፎ አልፎ ስለሚከሰት ብዙ ጭንቀት ሊያስከትል አይገባም ።**

## “herd immunity” ምንድን ነው፥ እንዴትስ ነው የሚሰራው?

“Herd immunity” ማለት **ሰዎች በተዘዋዋሪ መንገድ ከቫይረሱ የተጠበቁ ይሆናሉ ማለት ነው።** በተቻለን መጠን ብዙ ሰዎችን በመከተብ፡ ሌሎች ክትባቱን ያልወሰዱ ሰዎች፡ በቫይረሱ እንዳይያዙ እና ሊታመሙ እንደማይችሉ እናደርጋለን። **ከ 70-80% የሚሆኑ ሰዎችን መከተብ፡ ሌላው ሰው በበሽታው እንዳይያዝ በመከላከል “Herd immunity” ይሰጣል ብለን እናስባለን።**

## በዋትስአፕ ፣ በፌስቡክ እና በሌሎች ማህበራዊ ሚዲያዎች ብዙ መረጃዎች አሉ ። ትክክለኛውን ነገር እንዴት አውቃለሁ?

**እንደ ሀኪምዎ ወይም የነርስ** ባለሙያዎ ካሉ የታመኑ ምንጮች ወይም ኦንላይን ከ Public Health ድረገጾች መረጃዎችን ያግኙ (ከዚህ በታች ያሉትን ሊንኮች ይመልከቱ)።

## ለምን ያህል ጊዜ ይከላከልልኛል?

ክትባት ከተከተቡ በኋላ፡ ለምን ያህል ጊዜ በሽታውን እንደሚከላከልልዎ፡ በዚህ ጊዜ አናውቅም።

ተጨማሪ ጥያቄዎች ካሉዎት፡ ተጨማሪ የመረጃ ምንጮችን እና መረጃዎችን ሊሰጥዎ ከሚችል የህክምና ባለሙያ ጋር መነጋገር ይችላሉ። **እንዲሁም የሚከተሉትን የ Public Health ድረገጾችን መጎብኘት ይችላሉድረገጾች:**

1. https://covid-19.ontario.ca/covid-19-vaccines-ontario
2. https://www.canada.ca/en/public-health/services/diseases/coronavirus-disease-covid-19/vaccines.html